# አድርባይ ፖለቲከኞች

# ባፍንጫዬ ይውጡ!

ከ አቶሰውየው

*"ጀግና ይሙት እንጂ ፈሪ ይኑር ቢሻው፣*
*አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው ..."*

እኔ አቶሰውየው የዕድሜዬን አብላጫ ጊዜ በስደት ያሳለፍኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ። ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት በቦሌ ሳይሆን በባሌ ፤ ወድጄ ሳይሆን ተገድጄ በጊዜው የነበረው ፋሺሽታዊ መንግሥት ሀገሪቱ ያፈራቻቸውን ሊተኩ ያልቻሉ ወገኖችን በቀኝ በግራ በሚመትርበት ወቅት ትረፊ ያላትን ነፍሴን ብቻ አንጠልጥዬ በስደት ከተዳረጉ ወገኖች መካከል አንዱ ነኝ። ላለፉት ሠላሣ ዓመታት የሀገሬ ፖለቲካ በቅርብ የምከታተል ስለሆነ በሀገሬ ፖለቲካ ጠንጋራ ዝንብ እንኳ ቢወሳወስ ለይቼ አውቃለሁ ብል ማጋነን አይሆንም።

ይህንን በአድር ባይ ፖለቲከኞች ላይ ያለኝን አቋም የምገልጽበት ጽሁፍ ከማቅረቤ አስቀድሞ የደረሰብኝን ላጫውታችሁ ፥

ከምርጫ 97 ጥቂት ዓመታት በፊት ከተቃዋሚ ኃይሎች ወኪሎች ማለትም እነ ልደቱ ፣ ዶ/ር መራራ ጉዲና ፣ ክፍሌ አባተ ፣ ሌሎችም እንዲሁም ከኢሰመጉ ፕሮፌሰር መስፍን ባለሁበት ከተማ ሊመጡ ነው ሰምቼ ፤ እንደ አብዛኛው በውጪ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ያገሬ ጉዳይ አይሆንልኝምና ፣ ተነሳስቼ ወደ ስብሰባው ሄድኩኝ። ያው በበሩ ላይ በይፋ መግቢያ ክፈሉ ባይባልም ከጠረጴዛው ላይ ለተቀመጠው ሰው የሚደረገውን አድርጌ ከአዳራሹ ገብቼ ተቀምጥሁ። ስብሰባው ይጀመራል ከተባለው ሰዓት በጣም ዘግይቶ እንግዶቹ ገብተው መቀመጫቸውን ሲይዙ ተጀመሮ ፣ በጊዜው የነበረውን የሀገራችንን የፖለቲካ ሁኔታና የተቃዋሚዎችን ሚና ካብራሩ በኋላ እረፍት ሆኖ ስንመለስ የጥያቄና ምልልስ ጊዜ ሆኖ ታዳሚው አስተያየትም ጥያቄም ሲሰጥ እኔም እጄን አውጥቼ በጊዜው ማንም ያላነሳውን ታሥረው ደብዛቸው ስለጠፋት የፖለቲካ እስረኞች ስጠይቅ በመካከሉ የአቶ መለስ ዜናዊን ስም በአንቱታ ሳይሆን በአንተ ጠቅሼ አልፌ ነበርና በጊዜው መልስ ሊሰጡኝ ማይክሮፎኑን የያዙት እንግዳ ጥያቄዬ ላይ ከማተኮር ይልቅ አቶ መለስን አንቱ አለማለቴ አቶ መለስን ሳይሆን ያላከበርኩት የሕዝቡን ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እንደሆነ ወዘተ ወዘተ ... ብለው ወረደውብኝ ሲያበቁ ለጥያቄዬ የሚያመረቃ መልስ ሳይሰጡኝ ቀረ።

እኔም በሆዴ "ኸረ ተባለ እንዴ? የዛሬዎቹ ፖለቲከኞች ደግሞ ግብረገቡንም ገቡበት? አዬ ኢትዮጵያዬ!" ብዬ አዝኜ ጥያቄዬ እንዳልተመለሰ ባውቅም ስብሰባው ሳይበተን ሾልኬ ወደ ቤቴ ሄድኩኝ።

አዎ ያኔ በስብሰባ ላይ ሊያሳፍሩኝ የሞከሩት ፖለቲከኛ ዛሬ ማንነታቸውን ሕዝብ በግልፅ ያወቀው ፀሐይ የሞቃቸው አድር ባይ ከሃዲ ናቸው። ያኔም ከስብሰባው ወጥቼ ስሄድ በጊዜው የተሰበሰበውን ወገን በማክበር ነበር እንጂ ይሸረብልን የነበረው ጠፍቶኝ አልነበረም።

እንግዲህ ከዚያ በኋላ ምርጫ 97 መጥቶ ፤ በእኔ እምነት እንደነዚህ ባሉ አድር ባይ ከሃዲ ፖለቲከኞች ረዳትነት ወያኔ የሕዝቡን ድል ነጥቆ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይከፍሎ መስዋዕትነት ከፍሎ ፣ ዛሬ ታሥረው የነበሩ መሪዎቹ ተዋርደው ተፈተው የአንድነት ኃይሎች የምንሰባሰብበትን መላ እንፈጥር ይሆን ብለን በምናስብበት ወቅት እነሆ እነ ብርሃኑ ነጋና ብርቱካን ሚደቅሳ እነ አንዳርጋቸው ጽጌ ባለፉት ሁለት ዓመታት ያመሱን አልባቃችሁም ብለው በሚያሳዝን ሁኔታ ፤ ሁለት ዓመት መታሠራቸውን መስዋዕትነት ለአድርባይ ፖለቲካቸው አመቻችተው በዓለም መድረክ ብቅ በማለት በ97ቱ ምርጫ በዓለም ታዛቢዎች ፊት ክፉኛ ቆስሎ በጻዕረ-ሞት ላይ ያለን የወያኔዎች የዘረኝነት ሥርዓት የሕዝብ ወገንነት መልክ ለመስጠት ሲፏደሱ እየታዘብን ነው። የሁለት ዓመት እሥራቸውን ከሁሉ የሚበልጥ መስዋዕትነት አድርገው የጀግንነት ኒሻንቸውን አፍንጫችን ላይ ደግነው በክህደትና በውሸት የህገራችንን የፖለቲካ መስክ ለወያኔና ለደገፊዎቹ ለማመቻቸት የተቀጠሩ ለመሆናቸው ሳያፍሩን እየቀባጠሩ ይገኛል። ለዚህም ብርቱካን ሚደቅሳ ሰሞኑን በአሜሪካው ምክር ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ የፖለቲካ እሥረኞች ብዛት ስትመሰክር አንድ መቶ ናቸው እንዳለችው ዓይነት ፤ ብርሃኑ ነጋ በሰለጠነ ፖለቲካው በምርጫ 97ቱ ሕዝቡ ያሸነፈውንም ወያኔ ያጭበረበራቸውን ውንበሮች ለቀን አብረን እንሥራ ብለን ነበር ፤ ዛሬም ይሄንኑ ነው የምንግጠነው ብሎ ሳያፍር በየሄደበት ሙያ መስሎት ሲደሰኩር ሲመሰክር ያያችሁ የሰማችሁ ወገኖቼ ይህንን ዓይነት የጠራራ ፀሐይ ክህደት በይሉኝታ ልታልፉት አይገባም።

እነዚህ መሪ ተብዬዎች ኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል ወደ አሜሪካ ሲመጡ እንኳን መቀበል የተሳናቸው ፤ ካአንድነት ኃይሎች ጋር ከመነጋገርና የኢትዮጵያን ሕዝብ ዋይታ ለዓለም ከማስታወቅ ብሎም የዲሞክራሲውን ትግል ለማቀነባበር መሥራት ሲገባቸው በዛይድ ባሬ የጦር መኮንኖች ለሚመራው የኦጋዴን ናጻ አውጪ ነኝ ባይ በምስክርነት በዓለም አደባባይ ታዋቂነት ለማስጠት ሲራወጡ ላስተዋለ ምን ያህል ማፈሪያዎች መሆናቸውን ይገነዘባል። ለዚህም ነው እንደነዚህ ባሉ ባንዳዎች ላይ አቋም ይዤ ባፍንጫዬ ይውጡ የምለው። ወገኖቼንም የምጠይቀው ያመነታ ተመታ ነውና ሳታመነቱ እናንተም በነዚህ ጉዶች ላይ ዛሬውኑ አቋም ያዙ።

ይህ ሁሉ ሁኔታ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ቆም ብሎ ነገሮችን እንዲመረምርና በማያወላዳ ሁኔታ ቆማጣውን ቆማጣ ማለት የሚኖርበት ወቅት መሆኑን ያመለክታል። በኔ በኩል ለዘረኞች አንቱ የምለውም አልነበረም ፤ ዛሬም ደግሞ ለከሃዲዎች ፤ ላስመሳይ አድር ባይ ፖለቲከኞች አንተና አንቺም ሲበዛባቸው ነውና እንደጀግኖች እንኮኮ የምልበት ትከሻም ቄጠማም ጎዝጉዤ የምጎናበስበት ወገቡም የለኝምና አድር ባይ ፖለቲከኞች ባፍንጫዬ ይውጡ ነው የምለው።

ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ራዕይ አንግበው ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ፤ በኢትዮጵያዊነት ላይ በማንኛውም ዓይነት መልኩ በማንም ግፊት ሳይደራደሩ በጽናት የሚከፈለውን መስዋዕትነት እየከፈሉ ለሚያታግሉ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችም ሆነ ግለ ሰቦች ከፍተኛ አክብሮትና ድጋፌን ከመስጠት ወደ ኋላ አልልም። የተያያዝነው ትግል የዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ሀገር አድንም መሆኑን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ስለሆነም አንዳንድ ወገኖቼ እንደሚያደርጉት የቡድናዊ ጥብቆ (ማለያ) አጥልቄ ሳይሆን ነገሮችን የምመለከተው ፤ በሀገራችን የፍትህ መጉደል የሚያንገላታው እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ እንጂ ፤ በአማራው ላይ ብቻ ፣ ኦሮሞውን ነጥሎ ፣ ወይም ደግሞ በቅንጅት ላይ ብቻ ፤ በኢሕያፓ ላይ በተናጠል የመጣ አለመሆኑን ተገንዝቤ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተንሠራፋው የወያኔ የዘረኞች ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ ፣ እንዲያውም ከዚያ በፊት ከደደቢት ጀምሮ ለሠራቸው ጥፋቶች ፤ ለጨፈጨፋቸው ፣ ከምድረ-ገጽ ላጠፋቸው ተጠያቂነት ስላለበት ለነዚያ ወገኖች ሁሉ በተባበረ ድምፅ መጮህ እንዳለብን ሁላችንም ልንረዳው ያስፈልጋል እላለሁ።

በተናጠል ስንፍጨረጨር በተናጠል ከመመታት አንድንም። ወያኔም የሚፈልገውም ፣ የሚያሚቻችንም በተናጠል እንድንሰለፍለት ነው። እንዲያውም በወያኔ ላይ ሕዝባዊ ድል መጎናጸፍ ያቃተን እንቃወማለን የሚሉ ፖለቲከኞች (ሰሞኑን በየ ድረ-ገጾች ያብዛኛዎቹ ፎቶግራፎች ፣ አዎን ብርሃኑ ነጋና በየነ ጴጥሮስን ጨምሮ ከነመለስና ከኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ሻምፓኝ ሲራጨልን የሚያሳያውን መመልከት ይበቃል) የሚመሯቸው ድርጅቶች በሙሉ ኃይላቸውን አስተባብረው እንዳይታገሉ ጥቂት ግለ ሰቦች በሚፈጥሩት አምባ ጓሮ እየተውገረገረ መቆየቱ ነው።

ወያኔ ትንሽ ጥቅም እያቁለጨለጨ የሕዝቡን ትግል በተናጠል እንዲያስመቱ ያሰለጠናቸው ከማካከላችን እኛኑ መስለው እየተንቀሳቀሱ ለመሆኑ ሰሞኑን ላብዛኛው ወገኔ ግልጽ እየሆነ የመጣው የነ ብርሃኑ ነጋ ሴራ ምስክር ነው። ሕዝቡን እየነጣጠሉ አዘጋጅተው እየወሰዱ እንደ እሳት እራት ሊያስበንኑት!

እኛ ኢትዮጵያውያን ወያኔ ከሥልጣን ላይ ከወጣ ጊዜ አንስቶ በእያንዳንዱ ዓመት የተባበረ እንቅስቃሴ የምናደርግበትን መተማመንና መከባበርን በወያኔ ጋሻ ጃግሬዎች እርዳታ ቦርቡረን አምክነን እነሆ ዛሬ ከወያኔ የተዘጋጀልን ወጥመድ ወድቀን በመንፈራገጥ ላይ እንገኛለን። እንዴት ከዚህ ልንደርስ ቻልን ብለን እያንዳንዳችን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ራሳችንን ብንጠይቅና ጊዜ ሳንፈጅ መተማመንና መከባበርን እንዳ ሀገሬ ወጌሻ ለቃቅምን ከቦታው እንዲገባ መጠገን መጀመር ይኖርብናል። ይህ ጥረት ደግሞ እያንዳዳችን ትከሻ ላይ ወድቋል።

የመተማመን ግንባታው ከመጀመሩ በፊት ችግሩ ከየት ላይ እንደሆነ ማወቅን ይጠይቃል። በእኔ ግምት የችግሩ ዋና መሠረትና አቀናባባሪ የወያኔው ሥርዓት ቢሆንም ፤ እኛን እርስ በእርስ እንድንጠራጠር የሚያደርጉን የኛው ናቸው ብለን የምናምናቸው ፤ አንዳንዴም እያወቅናቸው የሚሠሩትን ደባ በጊዜ በይሉኝታ ባለማጋለጥና ባለማስተካከላችን በየጊዜው ለወያኔ እጅ መንሻ እያመቻቹን ሊታረድ እንደሚጎተት በግ በሞኝነት አምነን እንድንከተላቸው የሚያደርጉን ናቸው። ይህን ደግሞ የሚያደርጉት በአሉባልታና በወሬ ፤ ወያኔ ተቀምጦ በሕዝብ ወገኖችና ግለ ሰቦች ላይ የውሸት አፈ-ታሪክ በመንዛት ነው። ለዚህም እነ ኤልያስ ክፍሌና ተማሳሳይ ድረ-ገጾች ፣ የከረንት አፌርስ የፓልቶክ መድረክ ላለፉት ሁለት ዓመታት ያናፈሱትንና ሰሞኑን ከነ ብርሃኑ ነጋ ጋር በተቀነባበረ ሁኔት ያሚያዥጎደጉዱትን ማየት ይበቃል።

ጽሑፌን ከማጠቃለሌ በፊት ወገኖቼ እንዲያጤኗቸው የምፈልጋቸውንና ለሀቀኛ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች የሚከተሉትን ሃሳቦች ለማጋራት እወዳለሁ፥

1. ከወያኔ ጋር መደራደር በሀገራችን የዴሞክራሲን ሥርዓት መመሥረት አያስችልም። ወያኔ በታሪኩ ሁኔታዎች ወጠር ሲያደርጉት ለማዘናጋት እንደራደር ቢልም በመጨረሻ ቅራኔዎችን የሚፈታው በኃይል ብቻ ነው። ከወያኔ መደራደር የሕዝቡን ትግል እጅ ለማሰጠት ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ለሚደረገው የዴሞክራሲያዊ ትግል መሳካት ዋነኛው መሠረት የኃይል ሚዛንን ወደ ሕዝብ ወገን እንዲያጋድል የሚያደርግ ሕዝባዊ ጉልበት በጥንቃቄና በቁርጠኝነት ሲገነባ ብቻ ነው። ከዚያ ባነሰ አቅም መደራደር ሽንፈትን ለማረጋገጥ ነው።

2. ድርድር ተደርጎ ስምምነቶች እንዳይጣሱ የሚያስገድድ ነገር ቢኖር የኃይል ሚዛን የመኖር አለመኖር ጥያቄ ነው። ስለሆነም ከወያኔ ጋርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወክሎ እንዲሁም ከሌሎች እንደ ኦነግ ካሉ ድርጅቶች ማንኛውም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ እምነት ያለው የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ ግለ ሰብ ድርድር ከማድረጉ በፊት የኃይል ሚዛን ወደ ሕዝብ ወገን ማዘንበሉን ማረጋገጥ ያስፈልገዋል። ለዚህም ነው በቅንጅት ስም መሪዎቹ በእስር ባሉበት ወቅት የተደረገው የAFD ውል ኢትዮጵያዊ ኃይሎችን በቅንጅትም ውስጥ እንኳን ቢሆን በየቦታው የከፋፈለ ስለሆነ አሁኑኑ ሳይውል ሳያድር ቅንጅት ከዚያ ስምምነት መውጣት ወይም አለመውጣቱን ይፋ እንዲያደርግ የምጠይቀው።

3. ከላይ ለጠቀስኩት የኃይል ሚዛን ዝግጅት ፤ ቅንጅትና ኅብረትን ሌሎችንም ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ወደ አንድ ወገን ሊያሚጣ የሚችል ሥራ ባጣዳፊ መጀመር አለበት። ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያለንበት መተያየቱንና መፈራረቱን አብቅተን መተማመንን በአንድነት እንገንባ። ያኔና ያኔ ብቻ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በዓለም መድረክም ሆነ የትም ሊከበር የሚችለው ፣ ወያኔም እንደፈለገው ሊሸረው የማይችለው ድርድር ሊደረግ የሚችለው ፣ ያም ቢሆን ወንጀል ላልፈጸሙ ወያኔዎች እስከ ቦሌ ያለውን ምንገድ ለተወሰነች ጊዜ ክፍት ለማድረግ ብቻ!

ለዚህም ለቅንጅትም ሆነ ኅብረት አመራርና አባላት ከሁሉ በፊት አይን ለአይን ተያይተው ውይይት በማድረግ ያኃይል ሚዛኑን ወደ አንድነት ኃይሉ ወገን ሊቀይር የሚያስችል ብሔራዊ አጀንዳ እንዲነድፉ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹና በአስቸኳይ በግልጽ ሕዝቡን እያማከሩ ሥራ እንዲጀምሩ የምጠይቀው።

4. በተረፈ እያንዳንዳችን በዚህ ጽሑፌ እንዳሳየኋችሁ በከሃዲዎች ላይ ቁርጥ አቋም በመውሰድ እንደነ ብርሃኑ ነጋና ብርቱካን ሚደክሳ አይነቶቹን ከሃዲዎችና አድርባይ ፖለቲከኞችች ባፍንጫችን ውጡ በማለት ከኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ ለአንዴም ለሁሌም ማባረር ያለብን።

በኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕትነት መነገዱ ይቁም!
ምን ጊዜም ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር ያቸንፋል!

አቶ ሰውየው ከአሜሪካ
(መስከረም 25, 2000)